# የ COVID-19 ምልክቶችዎን በቤትዎ ውስጥ ሆነው መከታተል

የ COVID-19 በሽታ ኖሮቦት ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖሩ ከሆነ፣ ህመሙን ቤት ውስጥ ላሉ ሌሎች ሰዎች የማስተላለፍ እድልዎ ከፍተኛ ነው። የ COVID-19 ህመም ተገኝቶቦት እና/ወይም ምልክቶች ካሎት፣ ቤትዎ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከህመሙ ለመከላከል የሚከተሉትን ጥቆማዎች ይከተሉ:

**1** **በማንኛውም ጊዜ ቤት ውስጥ በማንኛውም ሰው አካባቢ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ያድርጉ።**



**2** **በማንኛውም ጊዜ ቢያንስ የ6 ጫማ (2 ሜትር) አካላዊ ርቀትን ይጠብቁ።**



**3** **የጋራ የሆኑ እንደ ምግብ ማብሰያ ክፍል ወይም መታጠቢያ ቤትን በተለያየ ሰአት ይጠቀሙ። በየተጠቀሙ ቁጥር ወለሎችን ሁሌም ያጽዱ። የምግብ ማብሰያ እቃዎችን እና ወለሎችን በየተጠቀሙ ቁጥር ይጠቡ።**



**4** **በተለይ መታጠቢያ ቤትን የሚጋሩ ከሆነ፣ መስኮቶችን በመክፈት አየር እንዲገባና የአየር ዝውውር እንዲጨምር ያድርጉ።**



**5** **የበር እጀታዎች ወይም እቃ መደርደሪያዎች የመሳሰሉ በብዛት የሚነኩ ሁሉንም ቦታዎች ከተጠቀሙ በኋላ ሁሌም ያጽዱ።**




**6** **አብራችሁ ከምትኖሯቸው ሰዎች ጋር እንደ የምግብ ማብሰያ መገልገያዎች፣ ፎጣዎች እና የአልጋ ልብሶችን የመሰሉ የግል ንብረቶችን አይጋሩ።**



**7** **ምልከቶችዎትን ይከታተሉ። ምልክቶችዎት እየባሱ ከሄዱ፣ የጤና እርዳታ አቅራቢዎ ጋር ይደውሉ ወይንም ከሌሎት ደግሞ የኪንግ ካውንቲ የ COVID-19 የጥሪ ማእከል ጋር ይደውሉ።**



**8** **በተቻለ አቅም ለብቻው በተለየ ክፍል ውስጥ በመሆን ከዋናው ቤትዎ ይራቁ።**



**9** **ጽዳቱን የጠበቀ የአኗኗር ዘዴን ይከተሉ።  ሲያስሉ እና ሲያስነጥሱ አፎትን በሶፍት ወረቀት ወይንም በክንዶ የውስጥ ክፍል ይሸፍኑ። እጆትን በሳሙና እና በውሃ በተደጋጋሚ ይታጠቡ ወይም ቢያንስ 60% አልኮል ባለው አልኮልን መሰረት ባደረገ የእጅ ማጽጃ ይታጠቡ።**



January 1, 2024

Public Health
Seattle & King County

# COVID-19 ይዟቸው ቤት ውስጥ ላሉ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ

COVID-19 ከያዘው ሰው ጋር መኖር፣ በ COVID-19 ለመያዝ እጅግ አጋላጭ ከሚባሉት ሁነቶች መካከል አንዱ ነው። ምንም እንኳን ማህበራዊ ርቀቶትን በሚገባ ቢጠብቁና የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ቢያደርጉ፣ COVID-19 ከያዘው ሰው ጋር አብረው ሲኖሩ በ COVID-19 የመያዝ እድሎት ከሌሎች ሁኔታዎች አንጻር እጅጉን ይጨምራል።

COVID-19 ከያዘው ሰው ጋር የሚኖሩ ከሆነ፣ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች እንዲያደርጉ እንመክራለን፡

**1** **ዋና እንክብካቤ እንዲሰጥ አንድ ሰው ምረጡ። በ COVID-19 የተያዘው ሰው በቂ እረፍት እያገኘ እንደሆነ ያረጋግጡ። ለትኩሳት፣ የጉሮሮ መድረቅ እና አጠቃላይ ለሆነ ምቾት ማጣት በመድሃኒት መደብር ውስጥ ያለሃኪም ትእዛዝ የሚሸጡ መድሃኒቶችን ይጠቀሙ። ከእነርሱ የጤና እርዳታ አቅራቢ የሚሰጡ ትእዛዞችን ይከተሉ።**

**2** **በተለይ መታጠቢያ ቤትን የሚጋሩ ከሆን፣ መስኮቶችን በመክፈት አየር እንዲገባና የአየር ዝውውር እንዲጨምር ያድርጉ።**



**3** **የጋራ የሆኑ እንደ ምግብ ማብሰያ ክፍል ወይም መታጠቢያ ቤቶትን በተለያየ ሰአት ይጠቀሙ። በየተጠቀሙ ቁጥር ወለሎችን ሁሌም ያጽዱ። የምግብ ማብሰያ እቃዎችን እና ወለሎችን በየተጠቀሙ ቁጥር ይጠቡ።**




**4** **የበር እጀታዎች ወይም እቃ መደርደሪያዎች የመሳሰሉ በብዛት የሚነኩ ሁሉንም ቦታዎች ከተጠቀሙ በኋላ ሁሌም ያጽዱ።**



**5** **በቤትዎ ውስጥ ወይም  ከቤትዎ ውጪ ከሌሎች ሰዎች ጋር መሆን ካስፈለጎት የአፈና የአፍንጫ መሸፈኛ ያድርጉ።**



**6** **አብራችሁ ከምትኖሯቸው ሰዎች ጋር እንደ የምግብ ማብሰያ መገልገያዎች፣ ፎጣዎች እና የአልጋ ልብሶችን የመሰሉ የግል ንብረቶችን አይጋሩ።**



**7** **ምናልባት COVID-19 ይዞት ከሆነ ምልከቶችዎትን ይከታተሉ።**



**8** **ምናልባት COVID-19 ይዞት ከሆነ ምልከቶችዎትን ይከታተሉ።**



**9** **ጽዳቱን የጠበቀ የአኗኗር ዘዴን ይከተሉ።   እጆችን በሳሙና እና በውሃ በተደጋጋሚ ይታጠቡ ወይም ቢያንስ 60% አልኮል ባለው አልኮልን መሰረት ባደረገ የእጅ ማጽጃ ይታጠቡ።**



**10** **የ COVID-19 ምርመራ ያድርጉ።**
**በቤትዎ ውስጥ ያለው የ COVID-19 ታካሚ ራሱን/ራሷን መለያ ጊዜውን ከሚያጠናቅቅበት የመጨረሻው ቀን ጀምረው ራሶትን ያግልሉ።**



January 1, 2024

COVID-19 ለያዛቸው ሰዎች እንዴት እንክብካቤ ማድረግ እንዳለቦት ተጨማሪ ጥቆማዎች ለማግኘት፣ እባክዎ ይህንን ይጎብኙ፡ www.kingcounty.gov/covid/self-care  (ድህረ-ገጹ በእንግሊዘኛ ብቻ ነው ያለው)

Public Health
Seattle & King County